# በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሰላም፤ አንድነትና እድገትን ስለ ማጠናከር ስልት

ኪዳኔ ዓለማየሁ

## ዓላማ፤

የዚህች ጽሑፍ መሠረታዊ ዓላማ፤ በእግዚአብሔር ቸርነት፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፤ ሙሉ ሰላምና አንድነት ተጎናጽፋ፤ እምነቷና አገልግሎቷ በዓለም ዙሪያ ተስፋፍቶ፤ ልማቷና እድገቷ እንዲጠናከር ለማድረግ የሚጠቅም የስልት ሀሳብ ለማቅረብ ነው።

## ተጨባጭ ሁኔታ፤

ለቸሩ አምላካችን ምሥጋና ይድረሰው እና፤ ቤተ ክርስቲያናችን፤ ብዙ በጎና አኩሪ ገጽታዎች የሚንጸባረቁባት ክርስቲያናዊ ድርጅት ናት። በመጽሐፍ ቅዱስ፤ የሐዋ. ሥራ፤ ም8/26-39፤ እንደ ተረጋገጠው፤ ክርስቲያንነት ወደ ኢትዮጵያ የዘለቀው፤ ከጥንት ጀምሮ (በ34 ዓ/ም) መሆኑ የታወቀ ነው። ስለዚህ፤ ጥንታዊነቷ፤ ቀጥተኛነቷ፤ ትውፊቷና እጅግ ሰፊ ትምሕርቷ ለሰው ልጅ ሁሉ ጠቃሚነቱና የነፍስ መዳኛ ሊሆን እንደሚችል አይጠረጠርም። በልዩ ልዩ ምክንያቶች በውጭ ሐገሮች የሚገኙት ካሕናትና ምእመናን፤ ለእምነታቸው ቅድሚያ በመስጠት በየሐገሩ፤ ቤተ ክርስቲያን በማቋቋም፤ ተዋሕዶ ኦርቶዶክሳዊነት እየተስፋፋ ይገኛል። ይህ ያላቋረጠ መስፋፋት፤ በበጎ በኩል የሚታይ ክስተት ነው።

በሌላ በኩል፤ እጅግ አሳሳቢ የሆነው፤ በቤተ ክርስቲያናችን ላይ ተጋርጦ የሚገኘው ክፉ አባዜ ግን፤ ከሀያ ዓመት በላይ ተከስቶ የሚገኘው፤ አሳዛኝ መከፋፈልና የእርስ በርስ መናቆርና መወጋገዙ ጉዳይ ነው። እንደሚታወቀው፤ ሐገር ውስጥ የሚገኘው ሲኖዶስና ከሐገር ውጪ የተፈጠረው፤ "ሕጋዊ ነኝ" የሚለው ሌላው ሲኖዶስ ተለያይተውና ተወጋግዘው ይገኛሉ። "ገለልተኛ" መሆኑን የሚገልጽ ሌላ ሶስተኛ ወገንም አለ። በዚህ መሠረት፤ ብፁዓን አባቶች ብቻ ሳይሆኑ፤ ካሕናትና ምእመናንም እጅግ በሚያሳዝንና አንገት በሚያስደፋ ደረጃ፤ መራራቁን፤ መነቃቀፉን፤ መተነኳኮሉን፤ ወዘተ፤ ተያይዘውታል። ሽምግልና ዋጋ ስላልተሰጠው፤ ቤተ ክርስቲያናችን የእልህ መፈንጪያ ሆና ትገኛለች።

መለያየቱና መወጋገዙ፤ ለቤተ ክርስቲያናችንም ሆነ ለውድ ሐገራችን፤ ለኢትዮጵያ፤ ከጉዳት ሌላ የሚያስገኘው፤ ውሱን ከሆነ ያውም ለጥቂት ሰዎች፤ ዓለማዊ ጥቅምና ሥልጣን ከማስገኘት ሌላ ምንም የሚፈይደው ነገር እንደ ሌለ በመገንዘብ፤ ዕርቀ ሰላም ለማውረድ መጠነኛ ጥረት ቢደረግም፤ እስካሁን አልተሳካም። ባሁኑ ጊዜ ተከስቶ የሚገኘው ሁኔታ፤ አራተኛው የዕርቀ ሰላም ጉባኤ፤ ጥር 16-18 ቀኖች 2005 ዓ/ም ሎዛንጀለስ እንዲከናወን ከታቀደ በኋላ፤ ሐገር ቤት የሚገኘው ሲኖዶስ፤ የጉባኤው ውጤት ከመታወቁ በፊት፤ ስለ 6ኛው ፓትሪያርክ ምርጫ፤ የአስመራጭ ኮሚቴ ሰይሟል። ስለዚህ፤ ይህ ሲኖዶስ፤ ጥር 6 ቀን 2005 ዓ/ም ሊያከናውን ባቀደው ጉባኤ፤ ሒደቱን ወደ ዕርቀ ሰላሙ ካልመለሰው፤ የቤተ ክርስቲያኗ መከፋፈል እንደሚቀጥልና ብዙ ጠንቆችንም እንደሚያባብስ ያሰጋል።

አንድ፤ በግልጽ መቀመጥ ያለበት ፍሬ ነገር፤ በቤተ ክርስቲያናችን የተከሰተው መከፋፈል፤ በዶግማ በመለያየት ሳይሆን፤ በአንዳንድ አባቶች የሥልጣንና የጥቅም ሽኩቻና፤ የዓለማዊ ፖለቲካ ጣልቃ ገብነት መሆኑን ነው።

## መከፋፈሉ ያስከተለውና የሚያባብሰው ጠንቅ፤

ተከስቶ የሚገኘው እጅግ አሳዛኝና አሳፋሪ መከፋፈል ካልተገራ፤ በቤተ ክርስቲያናችንና በሐገራችን ላይ የተጋረጡትን ጠንቆች እንደሚያባብስ አይጠረጠርም። ለምሳሌ ያህል፤ የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል፤

### 1ኛ/ **የአክራሪዎች ጥቃት፤**

ቤተ ክርስቲያናችን የምትመካው በእግዚአብሔር ኃይል ድጋፍ ቢሆንም፤ በመከፋፈል ከተዳከምን፤ ለአክራሪ አጥቂዎች ምቹ እንደምንሆን መታወቅ አለበት። በቅርቡ በሐገራችን የተከሰቱት፤ የገዳሞችና የደብሮች መቃጠል፤ የአንዳንድ ካሕናትና ምእመናን መገደል፤ የማይረሳ ነው። በቀድሞ ዘመኖች፤ የክርስቲያን አካባቢዎች የነበሩት፤ ግብጽ፤ ሶሪያ፤ ተርኪ፤ ወዘተ፤ ሊታሰቡ ይገባል። አንዳንድ የእስላም ሐገሮች ኢትዮጵያን እንደ በሰለች ብርቱካን በመቁጠር እጃቸው ውስጥ ለማስገባት እንደሚጥሩ ይነገራል። በዚህም መሠረት፤ በገንዘብና በሌላም ልዩ ልዩ ዘዴዎች፤ ዓላማቸውን ለማሳካት ጥረታቸውን እየቀጠሉ እንዳሉ የታወቀ ነው። ለዚህም ማስረጃ ካስፈለገ፤ ባለፉት 20 ዓመቶች፤ ኢትዮጵያ ውስጥ የተገነቡትን መስጊዶች ቁጥር ብቻ መመልከት በቂ ነው። በቤተ ክርስቲያናችንና በሐገራችን ላይ ከተጋረጡት ከባድ ችግሮች ግዙፉ ይኸው መሆኑን በቅድሚያ መገንዘብ አስፈላጊ ነው።

### 2ኛ/ **ለደብሮች፤ ገዳሞችና የአብነት ት/ቤቶች ስለሚያስፈልገው እርዳታ፤**

በሐገራችን የሚገኙ ብዙ ደብሮች፤ ገዳሞችና የአብነት ትምሕርት ቤቶች ሰፊ ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል። በማሕበረ ቅዱሳን ድርጅት በተዘጋጀ አንድ መጽሔት እንደ ተዘገበው፤ ከ100 በላይ ደብሮች፤ ድጋፍ በማጣት ምክንያት፤ ተዘግተዋል። ለዚህ አሳዛኝ ክስተት ምክንያቱ፤ በሐገራችን ያለው ድሕነትና በቤተ ክርስቲያን የተንሰራፋው ሙስና መሆኑ ተገልጿል። በተጨማሪ፤ ውጪ ሐገሮች የምንገኝ ኢትዮጵያውያን፤ በየዓመቱ፤ ወደ ኢትዮጵያ የምናስተላልፈው ገንዘብ ከ$3 ቢሊዮን ዶላር እንደማያንስ የታወቀ ሆኖ ሳለ፤ በተከሰተው መናቆርና መከፋፈል ምክንያት ለቤተ ክርስቲያን የምናበረክተው እርዳታ እጅግ አነስተኛ መሆኑ ያሳዝናል።

3ኛ/ **<u>የቤተ ክርስቲያናችን የልማት አስተዋጽኦ፤</u>**

እንደሚታወቀው፤ በድሕነትና በደዌ የተጠቃው ወገናችን፤ በአለኝታነት የሚጠጋው፤ አንደኛው አካባቢ፤ ቤተ ክርስቲያናችንን ነው። ባጋጠመው መከፋፈል ምክንያት፤ ቤተ ክርስቲያናችንን ያማከለ፤ የልማትና የእርዳታ ተግባር በሚፈለገው ደረጃ ሊከናወን አልቻለም። ምንም እንኳ፤ ቤተ ክርስቲያናችን ለአንዳንድ የልማት ተግባሮች አስተዋጽኦ ያደረገች መሆኑ ቢታወቅም፤ ካላት የምእመናን ቁጥር ጋር ሲመዛዘን በቂ ነው ሊባል አይችልም። ስለዚህ፤ መለያየቱ፤ የሐገራችንን ድሕነት፤ በተባበረ የልማት ተግባር፤ ለመቅረፍ አልተቻለም ማለት ነው።

4ኛ/ **<u>የምእመናን ቁጥር፤</u>**

በቅርቡ፤ በኢትዮጵያ በተከናወነው፤ የሕዝብ ቆጠራ፤ የቤተ ክርስቲያናችን ምእመናን ቁጥር ከሌሎች እምነት ተከታዮች ቁጥር ጋር ሲወዳደር፤ የእድገቱ መጠን በመቶኛ አኃዝ ዝቅ ማለቱ ተዘግቧል። ለዚህ ሁኔታ እንደ ምክንያት የሚጠቀሱት፤ የቤተ ክርስቲያናችን ስብከት ደረጃና፤ የኢኮኖሚ እርዳታዋ ድክመትና የሌሎቹ እምነቶች ኃይለኛ እንቅስቃሴዎች ናቸው። ለወደፊቱም ይህ አዝማሚያ እየባሰ እንዳይሔድ ከተፈለገ፤ ተጋርጦ የሚገኘው መከፋፈል መቋረጥ አለበት።

5ኛ/ **<u>የቤተ ክርስቲያናችን ዓለም-አቀፋዊነት፤</u>**

የቤተ ክርስቲያናችን ትምሕርት አስፈላጊነቱ፤ ለኢትዮጵያውያንና ለትውልደ-ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን ለዓለም ሕዝብ መሆኑ የታወቀ ቢሆንም፤ እስካሁን ድረስ፤ እንደ ሌሎቹ ሃይማኖቶች፤ በልዩ ልዩ የዓለም ቋንቋዎች የመጠቀም ሥልት አልተጀመረም። ለምሳሌ፤ የቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ፤ ስብከትና ትምሕርት በእንግሊዝኛ፤ በፈረንሳይኛ፤ በስፓኒሽኛ፤ በዓረብኛና በሌሎቹም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በሚጠቀምባቸው የዓለም ቋንቋዎች ቢቀርብ፤ ለቤተ ክርስቲያናችንና ለሐገራችን በሚጠቅም ደረጃ ከፍ ያለ የአማኞች ቁጥርና ድጋፍ ማግኘት ይቻል ነበር። በተጨማሪም፤ እንደ አሜሪካና አውሮፓ ባሉ፤ ብዙ ምእመናን በሚገኙባቸው አካባቢዎች፤ የቤተ ክርስቲያናችንን የትምሕርት ማእከሎች/ኮሌጆች ማቋቋም ይቻል ነበር። ነገር ግን፤ እንደዚህ ያለ ተግባር ለማከናወን፤ ሙሉ ሕብረትና ብቃት ያለው አመራር ያስፈልጋል።

6ኛ/ **<u>የማሕበሮች አለመተባበር፤</u>**

ከተጋረጡት እጅግ አሳዛኝና አስከፊ ክስተቶች ውስጥ ሊጠቀስ የሚገባው፤ እርስ በርስ የሚፋጩ ማሕበሮች ተፈጥረው፤ በልዩ ልዩ መገናኛ ብዙኃን (ድረ-ገጽ፤ ሬዲዮ፤ ጋዜጣ፤ መጽሔት፤ ስብከት፤ ወዘተ፤) ሲጣረዙ መመልከቱ ነው። አንዳንዶቹ፤ ያለአንዳች ሕፍረት፤ ባንድ በኩል በቤተ ክርስቲያናችን ስለ ተከሰተው መከፋፈል እያላዘኑ፤ በሌላ በኩል ግን፤ ራሳቸው፤ ሌላውን በማጥላላት ሲነቃቀፉ ይታያሉ። “መናፍቅ”፤ “ተሐድሶ”፤ “አክራሪ”፤ ወዘተ. እየተባባሉ ይወነጃጀላሉ። ይህ ሁኔታ ከሚጠቀሙባቸው ምክንያቶች አንደኛው፤ የሐሳብ ግጭት ሲከሰት፤ በተረጋጋ፤ በመከባበርና፤ በክርስቲያናዊ መንፈስ፤ መፍትሔ የማስገኘት (conflict resolution mechanism) ሥርዓትና ባሕል መዳከሙን ነው።

7ኛ/ **<u>የቀኖና መጣስ፤</u>**

ቀኖና የተጣሰው፤ በሁሉም በኩል መሆኑ በግልጽ ሊታወቅ ይገባል። ማስተካከሉም፤ እንደዚሁ፤ የሁለቱም በኩል ኃላፊነት ነው። አንድ ምሑር አባት፤ በግል በጻፉልኝ ማስታወሻ፤ ቅዱስ አትናቴዎስ አምስት ጊዜ (335-366 ዓ/ም) እንዲሁም ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ሁለት ጊዜ (347-407 ዓ/ም) ተሰደዋል። ነገር ግን፤ ሁለቱም ቅዱሳን አባቶች፤ ሲኖዶስ “ከኔ ጋር ተሰደደ” አላሉም። በተጨማሪም፤ ምሑሩ አባት እንደ ጻፉት፤”ሲኖዶስ የጣት ቀለበት አይደለም፤ በጣት ተጠልቆ ይዘውት ሊሄድ አይችልም። ....ሲኖዶስ ማለት መንፈስ ቅዱስ ማለት ነው። (የሐዋርያት ሥራ ም 15/28)።” በሌላ በኩል፤ በሐገር ቤት የተከናወነው፤ በፓትሪያርክ ላይ ፓትሪያርክ መሾም የቤተ ክርስቲያንን ቀኖና የጣሰ መሆኑ በይፋ የታወቀ ነው። የአቡነ ቴዎፍሎስ ሁኔታ በይፋ ሳይታወቅ የተከናወኑት የፓትሪያርክ ምርጫዎችና አቡነ መርቆሬዎስ በሕይወት፤ በጤና እያሉ የተፈጸመው የፓትሪያርክ ምርጫ፤ በፍትሕ መንፈሳዊው ድንጋጌ መሠረት፤ ከቀኖና ውጪ የሆኑ ድርጊቶች እንደ ነበሩ ግልጽ ነው።

8ኛ/ **<u>የፓትሪያርክ አመራረጥ ሥርዓት ውሱንነትና የመንግሥት ጣልቃ-ገብነት፤</u>**

የቤተ ክርስቲያናችን የፓትሪያርክ አመራረጥ ሥርዓት እጅግ ውሱን በመሆኑ፤ ለመንግሥት ጣልቃ-ገብነት ምቹ ሆኗል። ስለዚህ በንጉሡ፤ በደርግና ባሁኑም ዘመኖች፤ መንግሥት በፓትሪያርክ ምርጫ እጁን እንደሚያስገባ የታወቀ ነው።

9ኛ/ **<u>በኢየሩሳሌም የሚገኘው፤ “ዴር ሡልጣን” ገዳም፤</u>**

ከሰሃራ በታች ከሚገኙት ሐገሮች ውስጥ፤ እሥራኤል ውስጥ ታሪካዊ ንብረቶች ያላት ኢትዮጵያ ብቻ ናት። ከነዚሁ ቅርሶች ውስጥ፤ እጅግ ታዋቂ የሆነው፤ ታሪካዊው ቅርሳችን፤ “ዴር ሡልጣን” የተሰኘው ገዳማችን፤ ጥገና ስላልተከናወነለት፤ በመፍረስ ላይ

እንደሚገኝ ተረጋግጧል። ጥገናው ያልተከናወነው፤ በኦቶማን ቱርኮች የአካባቢው አገዛዝ ዘመን በተደነገገው የባለህ እርጋ (status quo) ውሳኔ መሠረትና ሕጋዊ ባልሆነ የይገባኛል ጥያቄ መሠረት፤ የግብጽ ኮፕቶች ጥገናውን ስለሚቃወሙና የእሥራኤል መንግሥትም ይህንኑ አቋማቸውን ስለሚደግፍ ነው። ይህም ከባድ ችግር፤ በቤተ ክርስቲያናችን በተከሰተው መናቆር ምክንያት፤ በቂ ትኩረት አላገኘም። ለዚህ አሳፋሪ ሁኔታ እንደ ማስረጃ ሊቆጠር የሚገባው፤ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ዓለም አቀፍ የምእመናን ማሕበር አማካኝነት፤ ገዳሙ እንዲጠገን እንዲፈቅዱ ለእሥራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር የተጻፈው፤ በማሕበሩ ድረ-ገጽ በwww.eotcipc.org ላይ የሚታየው የአቤቱታ ደብዳቤ ከአምስት ዓመት በኋላ፤ እስካሁን የተፈረመው ቁጥር እጅግ አነስተኛ ሆኖ መገኘቱ ነው!

10ኛ/ **<u>የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር መሻሻል አስፈላጊነት</u>**፤

ቤተ ክርስቲያናችን፤ ከዘረኛነት፤ ከሙስናና ከአሠራር ጉድለት ተላቅቃ፤ ግልጽነትና የውስጥ ቁጥጥር የሰፈነባት፤ ቀልጣፋ የመንፈሳዊ ድርጅት እንድትሆን ከተፈለገ፤ ሕጓ፤ አስተዳደሯ፤ እቅዷና መርሐ ግብሮቿ፤ ወዘተ፤ በጥልቀት ተመርምረው መሠረታዊ ለውጥና መሻሻል ያስፈልጋቸዋል።

11ኛ/ **<u>በምእመናን ችግሮች ላይ በቂ ትኩረት አለመኖሩ</u>**፤

አባቶች፤ በመከፋፈሉ ችግር ስለ ተወጠሩ፤ በምእመናን ላይ ተጋርጠው ለሚገኙ እጅግ ከባድ ችግሮች ደራሽ በመሆን ለመርዳት አልቻሉም። ለዚህ ሁኔታ፤ እንደ ምሳሌ ሊቀርብ የሚገባው፤ በቤተ ክርስቲያናችን ቅዳሴ መሠረት፤ አብዝኛዎቻችን (90%) ምእመናን የእግዚአብሔርን ሕግ አፍራሾች ሆነን መገኘታችን ነው። እንደሚታወቀው፤ በቅዳሴው መጀመሪያ ላይ፤ እኛው ምእመናን፤

> "ሃሌሉያ፤ በቅዳሴ ጊዜ ከምዕመናን ወገን ወደ ቤተ ክርስቲያን የገባ ሰው ቢኖር፤ ቅዱሳት መጻሕፍትን ሳይሰማ፤ የቅዳሴው
>
> ጸሎት እስኪፈጸም ባይታገሥ፤ ከቁርባኑም ባይቀበል፤ ከቤተ ክርስቲያን ይለይ፤ የእግዚአብሔርን ሕግ አፍርሷልና።"

እያልን አዋጁን እናዜማለን። የቅዳሴው ዋና ዓላማ፤ ቅዱስ ቁርባኑን ለመቀበል ሆኖ ሳለ፤ ለነፍስ መዳኛ የሚያስፈልገንን ሳንቀበል እየቀረን ሥጋ ወደሙን እያጠናቀቁ የሚገኙት ካሕናቱ ራሳቸው ሆነው መገኘታቸው እጅግ አሳሳቢ ጉዳይ ሆኖ ሳለ ለዚህ ከባድ ችግር ቅድሚያ በመስጠት፤ ባለጉዳዮቹን ምዕመናንን በመጠየቅ፤ ጥልቅ ጥናት በማከናወን ተገቢ የሆነ ለዘለቄታው የሚበጅ መፍትሔ ማስገኘት አልተቻለም። ስለዚህ ጉዳይ፤ ይህ ጸሐፊ፤ በየደረጃው፤ ለአባቶች ያቀረበው አቤቱታ እስካሁን በቂ መልስ አላገኘም።

**<u>የመፍትሔ ሐሳቦች</u>**፤

1ኛ/ **ለአጭር ጊዜ** (3 ዓመት)፤

(ሀ) **<u>ሽምግልናና የምእመናን ሚና</u>**፤

የተጀመረው የዕርቀ-ሰላም ሒደት፤ ቢሳካም ባይሳካም፤ በሁሉም ወገኖች በኩል የሚከበሩ የሽማግሌዎች አካል በመፍጠር፤ በቤተ ክርስቲያናችን፤ ሰላም፤ አንድነትና ፍቅር እንዲሰፍንና በሁሉም ደረጃዎችና አሕጉሮች እንዲሰርጽ ማድረግ ያስፈልጋል። ቤተ ክርስቲያን የምእመናንም ስለ ሆነች፤ እንደዚህ ስትታመስ፤ ተመልካች ብቻ መሆን የለብንም። ቁርጠኛ እርምጃ በመውሰድ፤ በቤተ ክርስቲያናችን ሰላም፤ አንድነት፤ ፍቅርና እድገት እንዲሰፍን፤ ምእመናን ግዴታችንን መወጣት አለብን። ለበለጠ ዝርዝር፤ www.eotcipc.org ይመልከቱ።

(ለ) **<u>ውግዘቱን ስለ ማንሳት</u>**፤

በፍትሐ ነገሥት፤ አንቀጽ 9፤ ቁጥር 338፤ እንደሚከተለው ተደንግጓል፤

> "ከተወገዘው ወይም ከተለየው ጋር የተነጋገረ ውይም ከነርሱ ጋር የጸለየ ከቤተ ክርስቲያን ይለይ።" ይላል።

ስለዚህ፤ ከሐገር ውስጥም ከውጭም የተወከሉት የሰላም ልዑካን፤ ዳላስ፤ ቴክሳስ፤ በሚገኘው ቅዱስ ሚካኤል ካቴድራል፤ አብረው የተነጋገሩና የጸለዩ ስለ ሆነ ውግዘቱን፤ በሁለቱም በኩል የሚገኙት ብፁዓን አባቶች በአስቸኳይና በይፋ አስወግደው ለካሕናትና ለምእመናን ሰላምና አንድነት ማጎናጸፍ ያስፈልጋል።

(ሐ) **<u>የቤተ ክርስቲያንን አንድነት ስለ ማስገኘት</u>**፤

ባሁኑ ጊዜ፤ ቤተ ክርስቲያናችን መስቀልኛ መንገድ ላይ ትገኛለች። ያሉት ግልጽ አማራጮች፤ በሕይወት የሚገኙትን ፓትሪያርክ፤ አቡነ መርቆሬዎስን ወደ መንበራቸው በመመለስ፤ አንድነትን ማስፈን፤ ወይም፤ ሌላ ፓትሪያርክ በመምረጥ ቤተ ክርስቲያናችን ለሁለት ተከፍላ እንድትቀጥል ማድረግ ነው። ከላይ፤ በተራ ቁጥር 7 የተጠቀሰውን የቀኖና መጣስ ከመቀጠል፤ ባሁኑ ጊዜ ባጋጠመው ልዩ ሁኔታ

በመጠቀም፤ በተለይም፤ በፍትሐ ነገሥቱ፤ በአንቀጽ 4፤ ቁጥር 77 እና 78 መሠረት፤ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን፤ አንድነት፤ ሰላምና ፍቅር ማስገኘት፤ የአባቶች መንፈሳዊና ታሪካዊ ግዴታ ነው። ይህንን ሁኔታ ለማመቻቸት፤ በቅድሚያ የሚያስፈልግ አንድ ከባድ ጉዳይ አለ። ይኸውም፤ የብፁዕ አቡነ መርቆሬዎስ የተሟላ መሆኑንና ወደ መንበራቸው ለመመለስ ፍላጎታቸው መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

(መ) <u>ስለ ሃይማኖቶች መቻቻልና መከባበር</u>፤

በኢትዮጵያ የሚገኙት ሃይማኖቶች፤ በተለይ ኦርቶዶክሳውያንና እስላሞች፤ ተከባብረውና ተቻችለው፤ በሰላም እንዲኖሩ የመወያያ መድረክና የግጭት ማስወገጃ ሥልትና ሥርዓት እንዲኖራቸው ማቀናጀት ያስፈልጋል።

(ሠ) <u>የቤተ ክርስቲያናችንን ትምሕርትና ስብከት ስለ ማጠናከር</u>፤

በሐገራችን፤ የምእመናን ግንዛቤና ቁጥራቸውም እንዲዳብር፤ የካሕናትና የዲያቆናት ሥልጠና በስፋት ቢከናወን፤ እንዲሁም በሌሎች ሐገሮች የቤተ ክርስቲያናችን ትምሕርት እንዲስፋፋ፤ በልዩ ልዩ ቋንቋዎች፤ ለምሳሌ በእንግሊዝኛ፤ ለማስተማር በቂ ዝግጅት ተደርጎ ተግባሩ እንዲጀመር ማድረግ ያስፈልጋል። በተጨማሪም፤ በሰሜን አሜሪካ፤ አንድ የቤተ ክርስቲያናችን ኮሌጅ እንዲከፈት ያስፈልጋል።

(ረ) <u>ለቤተ ክርስቲያን ስለሚያስፈልገው እርዳታና የልማት አስተዋጽኦ</u>፤

የቤተ ክርስቲያናችን አንድነት እንደሚሰፍን በማመን፤ ለገዳሞች፤ ለደብሮችና ለአብነት ትምሕርት ቤቶች የሚያስፈልገው እርዳታና ተጨማሪ ግንባታ፤ እንዲሁም፤ በሐገራችን ተንሰራፍቶ ስለሚገኘው ድሕነትና የጤና ችግር፤ ባለው አቅም ሊከናወን የሚችለውን፤ በልማት መርሐ ግብር ሥልት፤ ለአጭር፤ ለመካከለኛና ለረጅም ዘመን የሚያስፈልገው እቅድ እንዲዘጋጅና እንዲተገበር ያስፈልጋል። ይህንንም ለማከናወን፤ ብቁ ችሎታ ያለው የቤተ ክርስቲያን ድርጅትና የሰው ኃይል ያስፈልጋል። በዚህም መሠረት፤ በዓለም ሙሉ ያሉት ደብሮች፤ እያንዳንዳቸው፤ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ እንዲመደብና ተግባራዊ እንዲሆን ያስፈልጋል።

(ሰ) <u>ማሕበሮችን ስለ ማስተባበርና ለሐሳብ ልዩነቶች መፍትሔ ስለ ማግኘት</u>፤

በቤተ ክርስቲያናችን ሰም የሚንቀሳቀሱት ማሕበሮች የሚመዘገቡበትና እውቅና አግኝተው አገልግሎታቸውን የሚያበረክቱበት፤ ገንቢ የሆነ ሥርዓት ያስፈልጋል። የሐሳብ ልዩነት ሲከሰትም፤ በሰላማዊ ውይይት፤ በቤተ ክርስቲያን ዶግማና ቀኖና መሠረት፤ በሊቃውንት ትንተና፤ መፍትሔ የሚገኝበት ሥርዓትና ችሎታ ያስፈልጋል።

(ሸ) <u>ስለ የሥልጣን እርከኖች መስፈርትና የምርጫ/የሹመት ሥርዓት ማጠናከር</u>፤

ከፓትሪያርክ እስከ ዲያቆን፤ በቤተ ክርስቲያናችን ላሉት የሥልጣን እርከኖች፤ ግልጽ የሆነ፤ የተሟላ፤ መስፈርት፤ በጽሑፍ እንዲሰራጭ ያስፈልጋል። የምርጫና የሹመቱ ሥርዓትም ጣልቃ-ገብነትንና ሙስናን በማያመቻች ሁኔታ፤ በመንፈሳዊነታቸውና አስፈላጊ በሆነው እውቀትና በሌላውም ሁሉ ብቁ የሆኑ ብቻ እንዲሰየሙ የሚያደርግ እንዲሆን ያስፈልጋል። ለምሳሌ፤ የግብጽ ኮፕቶችና የኛው የፓትሪያርክ አመራረጥ ሥርዓቶች ሲነጻጸሩ፤ የትኛው ጣልቃ-ገብነትን እንደማያመቻች በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል። የቤተ ክርስቲያናችን የምርጫና የሹመት ሥርዓት በአስቸኳይ መሻሻልና መጠናከር ያስፈልገዋል።

(ከ) <u>የቤተ ክርስቲያናችን የአስተዳደር ሕግና መዋቅር</u>፤

ለቤተ ክርስቲያናችን እድገትና ልማት፤ ለዓላማዎቿ መሳካት፤ እንዲሁም ግልጽነት፤ ቁጥጥርና ቅልጥፍና የሰፈነበት፤ ከሙስና የተላቀቀ ሥርዓት እንዲኖር፤ ብቁ የሆነ የአስተዳደር ሕግና መዋቅር ያስፈልጋታል። ስለዚህ፤ ቃለ አዋዲውና ሌሎችም የውስጥ ደንቦች፤ በባለሞያዎች በጥልቅ ተጠንተው ተገቢውን መሻሻል የሚያስገኝ ሰነድ ለቅዱስ ሲኖዶሱ እንዲቀርብና እንዲጸድቅ ያስፈልጋል።

(ቀ) <u>ስለ "ዴር ሡልጣን" የኢትዮጵያ ገዳም ጥገና</u>፤

በኢየሩሳሌም የሚገኘው ገዳማችን፤ በአስቸኳይ የሚያስፈልገው ጥገና እንዲከናወንለት፤ እስካሁን ከተከናወነው እጅግ በጣም የላቀ የዲፕሎማሲ ጥረት ማድረግ ያስፈልገዋል። በየሐገሩ የሚገኙ ካሕናትና ምእመናን፤ ለሚኖሩባቸው ሐገሮች የመንግሥት ባለሥልጣኖች አቤቱታ በማቅረብ፤ እንዲሁም በwww.eotcipc.org ላይ የሚገኘውን ለእሥራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር የተጻፈውን የአቤቱታ ደብዳቤ በመፈረም፤ ለታሪካዊው ገዳም የሚያስፈልገው ጥገና እንዲከናወን ያላሰለሰ ጥረት መደረግ አለበት።

(በ) <u>በምእመናን ላይ ስለ ተከሰቱ ችግሮች</u>፤

በምእመናን ላይ ተጋርጠው ስለሚገኙ አንዳንድ ችግሮች፤ ለምሳሌ ስለ ቅዱስ ቁርባን እንዲሁም ሴቶችን፤ ለምሳሌ፤ የወርሀ-አበባን ስለሚመለከቱ ጉዳዮች፤ ተገቢው ምርመራና ጥልቅ የሆነ ጥናት ተከናውኖ ተገቢው መፍትሔ ለቅዱስ ሲኖዶስ ቀርቦ ከተወሰነበት በኋላ ተግባራዊ እንዲሆን ያስፈልጋል።

**ለመካከለኛና ለረጅም ዘመን**፤(4+ ዓመት) ከላይ፤ በአጭር ዘመን የሚዘጋጁትን፤ በቀጣይነት ተግባራዊ ማድረግና እንደ አስፈላጊነቱም፤ የማሻሻያ እቅዶችን አውጥቶ መተግበር።